# ክልል አቀፍ ምዘናዎች፥ ቤተሰቦች ACCESS እና Alternate ACCESS ውጤቶችን ስለመጠቀም ማወቅ የሚያስፈልጋቸው ነገሮች

በየዓመቱ፥ የእንግሊዘኛ ተማሪዎች (ELs) ተብለው የሚታወቁ የሚኒሶታ ተማሪዎች የፌደራል እና የስቴት መስፈርቶችን ለሟሟላት ከሚከተሉት የእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃት መመዘኛዎች ውስጥ አንዱን ይወስዳሉ፣ ይህም ከ MCA ወይም MTAS በተጨ ማሪ ነው፤

- ACCESS (ACCESS for ELLs)
- Alternate ACCESS (Alternate ACCESS for ELLs)

አብዛኛዎቹ ELs ACCESS ይወስዳሉ፣ ነገር ግን ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች የሚያገኙ እና የብቃት መስፈርቶቹን የሚያሟሉ ተማሪዎች ከዚያ ይልቅ Alternate ACCESS መውሰድ ይችላሉ።

የእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃት ምዝናዎች በእንግሊዘኛ ቋንቋ የንባብ፣ ማዳመጥ እና የመናገር ጎራዎች ተማሪዎ ስላለው እድገት መረጃ ይሰጣሉ።

ግላዊ የተማሪ ሪፖርት (ISR) የእያንዳንዱን ተማሪ የACCESS ወይም Alternate ACCESS ውጤቶችን ይሰጣል።




- ውጤቶቹ የተማሪዎ የእንግሊዘኛ ትምህርት እድገት አንዱ **መለኪያ** ነው፣ ይህም በ WIDA የእንግሊዘኛ ቋንቋ እድገት መስፈርቶች ውስጥ እንደተገለጸው ነው።
- ሪፖርቱ የእያንዳንዱን የቋንቋ ጎራ ውጤቶችን እንዲሁም እያንዳንዱ የብቃት ደረጃ ያለውን ትርጉም መግለጫ አካትቶ ይይዛል።
- ቅይጥ ውጤቱ የተፈተኑት አራቱን የቋንቋ ጎራዎች የተቀናጀ የብቃት ደረጃን ይወክላል። የቋንቋ ብቃት ደረጃ በማያቋርጠው የቋንቋ ክህሎቶች እድገት ላይ ተማሪዎች ያሉበትን ሁኔታ የሚለካ ነው። ተማሪዎች ከፍተኛው የቋንቋ ብቃት ደረጃዎች ላይ ሲደርሱ፣ ከዚያ በኋላ የቋንቋ ድጋፍ አገልግሎቶች አያስፈልጋቸውም።



ውጤቶቹ የተማሪዎች የቋንቋ ክህሎቶች በምን መልኩ እያደጉ መሆኑን **ለመከታተል** የሚያገለግሉ ናቸው።

- ትምህርት ቤቶች ውጤቶቹን ስለ እንግሊዘኛ ቋንቋ ፕሮግራሞች እና ትምህርት ውሳኔዎችን ለመወሰን መጠቀም ይችላሉ።
- መምህራኖች የእንግሊዘኛ ቋንቋ እድገትን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለመደገፍ ውጤቶቹን መጠቀም ይችላሉ።
- ACCESS ውጤቶች የእንግሊዘኛ ብቃትን ለመለየት እና ተማሪዎች ከ EL ፕሮግራሞች የሚወጡበትን ጊዜ ለመወሰን ያገለግላሉ።



ተማሪዎን መጠየቅ ያለብዎ ጥያቄዎች፥

- እንግሊዘኛ ስትማር/ሪ ያለህ/ሽ ጠንካራ ጎኖች ምንድን ናቸው እና ፈተና የሆነውስ ምንድን ነው?
- እርዳታ ለማግኘት ወይም ጥያቄ ለመጠየቅ ትምህርት ቤት ውስጥ ማዋራት የሚችሉት ማንን ነው?

የተማሪዎን መምህር መጠየቅ ያለብዎ ጥያቄዎች፥

- የተማሪየ እድገት ላይ ተጨማሪ ማሻሻያዎችን እንዴት ማግኘት እችላለሁ?
- በትምህርት ቤት ውስጥ ተማሪየን ሊያግዝ የሚችል ምን ድጋፍ አለ?

# ክልል አቀፍ ምዘናዎች ለሚኒሶታ የትምህርት እቅድ መረጃ ይሰጣል

## የመስፈርቶችን አፈጻጸም መከታተል

- እነዚህ መስፈርቶች የተማሪ የመማር እና የትምህርት ሂደት የሚጠበቁት ምን እንደሆነ ይወስናሉ።.
- ክልል አቀፍ ምዘናዎች ተማሪው መስፈርቶቹን በመማር ረገድ ያለውን ቅጽበታዊ ምልከታን ያሳያል።
- የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና ዲስትሪክቶች እነዚህን ውጤቶች የሚዛናዊ እና ሁሉን አቀፍ የምዝና ስርዓታቸው አንዱ አካል በማድረግ ይጠቀሙበታል።
- ከዲስትሪክቱ የምዘና ስርዓት (የመማሪያ ክፍል፣ ዲስትሪክት፣ እና የስቴት ምዘናዎች) የሚገኙ መረጃዎች በአንድነት መስፈርቱን የማስተማር እና የመማር ሂደቱን ያግዛሉ።

## ለፍትሃዊነት ቅድሚያ መስጠት

- ከሚዛናዊ እና ሁሉን አቀፍ የምዝና ስርዓት የሚገኝ መረጃ ዘራቸው ወይም የዚፕ ኮዳቸው ምንም ይሁን፣ እያንዳንዱ ተማሪ ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት ማግኘቱን ያረጋግጣል።
- የክልል አቀፍ ምዘና ውጤቶች ግልጽ ያልሆነ ኢፍትሃዊነት ያለበትን ቦታ ለመለየት እና ተስፋ ሰጭ የማስተማር ልማዶች ላይ ለማተኮር የተለያዩ የተማሪ ቡድኖችን፣ ትምህርት ቤቶችን እና ዲስትሪክቶችን ለመመልከት ሊረዳ ይችላል።

## የተረጋገጠ ውጤቶችን መስጠት

- የሚኒሶታ አስተማሪዎች እና የማህበረሰብ አባላት በርካታ ደረጃ ያለውን ፈተና በማዘጋጀት ላይ ተሳትፎ አላቸው እና በዚህ ሥራ ላይ ዋና አጋሮች ናቸው።
- ሪፖርት ከመደረጉ በፊት ጥብቅ ማጣሪያዎች እና ማረጋገጫዎች አሉ።
- እነዚህ ሁለቱም ክልል አቀፍ የምዘና ውጤቶች ተማሪዎቹ ፈተናውን በሚወስዱበት ጊዜ መስፈርቶቹን ስለመማራቸው የተረጋገጡ እና አስተማማኝ መለኪያዎች ናቸው።

ከማርች 2020 ጀምሮ፥ መምህራኖች እና ተማሪዎች በማስተማር እና በመማር፣ እንዲሁም በማህበራዊ እና ስሜታዊ ደህንነት ላይ ከፍተኛ እና ጉልህ ለውጦችን አስተናግደዋል። በመሆኑም እነዚህ ለውጦች በተማሪ ውጤት ላይ ሊንጸባረቁ የሚችሉ እና ነገር ግን በትክክል መለየት አስቸጋሪ ስለሆነ፣ የምዘና ውጤቶች ሲተረጎሙ ይህን ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው።

ጥያቄዎች?

የእንግሊዘኛ ተማሪዎች ትምህርት ቤትዎ ውስጥ ያላቸውን አፈጻጸም አስመልክቶ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ የ *ACCESS* for *ELLs Achievement Levels* ገጽን በ ሚኒሶታ ሪፖርት ካርድ ላይየሚገኘውን ይጎብኙ።

ስለ ተማሪዎ የ MCA ወይም MTAS ውጤቶች ጥያቄዎች ካሉት፣ ትምህርት ቤትዎን ያግኙ። ስለ ሚኒሶታ የአካዳሚክ መስፈርቶች ወይም ምዘናዎች ጥያቄዎች ካሉት፣ ያግኙ mde.testing@state.mn.us።

DEPARTMENT OF EDUCATION